# ሌላው የውጫሌ ውል (ከስንታየሁ አዲስ አበባ)

የወያኔው ሪፖርተር የዘገበውና እንዲህ ብሎ የሚጀምረው ሁነት ያጫረው ግጥም፡-
«የአሜሪካ መንግስት በአፍሪካ በሚያቋቁመው የአሜሪካ ወታደራዊ ዕዝ አፍሪኮም የአየር ሀይል ዋና ማዕከል ኢትዮጵያ አዲስ አበባ ላይ ሊሆን እንደሚችል የአሜሪካ አየር ሀይል ከፍተኛ ባለስልጣን መናገራቸውን የኤር ፎርስ ታይምስ ጋዜጣ ዘገበ። … እንደ ባለስልጣኑ ገለጻ ምንም እንኳ ውሳኔ ላይ ባይደረስም ከቀረቡት አማራጮች አዲስ አበባ በቀዳሚነት እየመራች እንደሆነ ጠቁመዋል። …»

2003ትን ውጫሌ እያላችሁ፣
የውጫሌውስ ውል፣ አሁን መጣላችሁ።

የአሜሪካ አየር ኃይል፣ ቋሚ መቀመጫ፣
ነፃነት ለጠማው፣ ፈጥኖ ደራሽ መቅጫ፣
ኢትዮጵያ ሆናለች፣ መጀመሪያ ምርጫ።
በኢትዮጵያ መሬት፣ ይሰራ ከተባለ፣
ከዚህ የሚከፋ፣ ውጫሌ ምን አለ?
ሉዐላዊት ሀገር፣ በአሜሪካ አየር ኃይል፣
ጥላ ስር ከዋለች፣
ምኑን ነፃ ሆና፣ ታሪኳን ጠበቀች?
«ቁጭ ብሎ መስቀሉ፣ ቀላል ሲመስላችሁ፣
ኋላ ቁሞ ማውረድ፣ እንዳይችግራችሁ፣»
ወይስ እንደ ዶሮ፣ ታፈሱት ጭራችሁ፣
እኛ ካልበላነው፣ ይበተን ብላችሁ።

ከአጋም የተጠጋ፣ ቁልቋል እንዳትሆኑ፣
ረጋ ብላችሁ፣ መዘዙን አጢኑ።

ታጋይ ነን ስትሉ፣ በማንነታችሁ፣
ምነው በራስ ማመን፣ ፈጽሞ አቃታችሁ?
እስከ መቼ ድረስ፣ ዘበኛ አቁማችሁ?

ረጅሙን ጉዞ፣ ትዘልቁት አላችሁ?
በግልጽ ይታያል፣ ተስፋ መቁረጣችሁ።

እንደ አያቶቻችሁ፣ እንደ አባቶቻችሁ፣
ምን አለ ብታልፉ፣ በማንነታችሁ?
ሳይሞት ሳይቀበር፣ ጥንተ ታሪካችሁ።

ምነው አቦይ ሥብሐት፣ ለሌላው ነፃነት፣
እንዲያ ሲፎክሩ፣
ለአሜሪካ አየር ኃይል፣ ኢትዮጵያን በነሲብ ልትቸረችሩ
ማን አለብንነት፣ አልበዛም ነገሩ?

ባህሩን ወደቡን፣ በነፃ ስጥታችሁ፣
አገሪቱን በሊዝ፣ ሸጣችሁ፣ ሸጣችሁ፣
አየሩንም ሳይቀር፣ ታጫርታላችሁ?
ምነው ከጋዳፊ፣ ልብ ቢሰጣችሁ?!

የአፍሪካ አርአያ፣ የነበረች አገር፣
እንዴት እንደዋዛ፣ በቁሟ ትቀበር?!
ሁሉ በእጃችሁ ነው፣ ሁሉ በደጃችሁ፣
ከሕሊና በቀር፣ ምን ጎደለባችሁ!
ትዝብት አታትርፉ፣ ሳይቀር ማለፋችሁ።

Posted on www.debteraw.com by courtesy of the author

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com